# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

## ሁለተኛው ትውልድ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም

### መጸዳጃ ቤት አሰራርና አጠቃቀም ፣ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ፣ አያያዝና አወጋገድ ፓኬጅ

ሐምሌ 2007 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ማውጫ


1. መግቢያ ..... 3

2. ዓላማ ..... 3

2.1. አጠቃላይ ዓላማ ..... 3

2.2. ዝርዝር ዓላማ ..... 3

3. ቁልፍ መልዕክቶች ..... 5

4. የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድና መጸዳጃ ቤት አዘገጃጀት አያያዝና አወጋገድ ፖኬጅ በሚመለከት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ..... 10

4.1. የቀበሌውን መረጃ መሰብሰብ ..... 10

4.2. በመረጃው የተሰበሰበውን ውጤት ለህብረተሰቡ መግለጥና በጋራ የሥራ እቅድ ማውጣት ..... 10

4.3. በተሻሻለ መፀዳጃ ቤት፣ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ላይ ስለጠና መስጠት ..... 10

4.4. ለፓኬጁ ስራ ደጋፊ ሊሆኑ ከሚችሉ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ ተቋማት፣ማኅበራዊ ተቋማት፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ቅንጅት በመፍጠር፣ ..... 10

4.5. ህብረተሰቡን በማስተማር፣ በማስተባበር፣ በመቀስቀስ ተሳትፎውን በማሳደግ የባህሪ ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ፤ ..... 11

4.6. ከአይነምድር ነፃ የሆነ ቀበሌ/መንደር/ጎጥ መፍጠር ..... 12

4.7. የተሻሻለ መጸዳጃ ቤትን ኅብረተሰቡ እንዲሠራ ለማድረግ አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን ማስተዋወቅ ..... 13

4.8. ሰርቶ ማሳያ ዘዴ በመጠቀም ዘላቂነት ያለው የተሻሻለ መፀዳጃ ቤት አሰራርና የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ክህሎትን ማስጨበጥ ..... 13

4.9. መልካም ተሞክሮን ማስፋፋት ..... 13

4.10. የማነቃቂያ ዘዴዎች በመጠቀም አመርቂ ውጤት ላመጡ አባዎራዎችና ልማት ቡድኖች ማበረታታቻ መስጠት ..... 14

4.11. አካባቢያዊና ሕጋዊ ደንቦችን በመጠቀም፣ ..... 14

5. አገልግሎቱ ለመሰጠት የሚያስፈልጉ ግብአቶች ..... 14

5.1. ማጣቀሻዎች ..... 14

5.2. ቁሳቁሶች ..... 14

1. ከጤና ጣቢያ ጋር አብሮ መስራት ..... 15

7. የሚጠበቁ ውጤቶች ..... 15

8. ድጋፋዊ ክትትልና ግምገማ መለኪያዎች ..... 16

## 1. መግቢያ

ቆሻሻ ሲባል በሁለት ዋና ዋና ምድቦች የሚከፈል ሲሆን እነዚህም ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ በመባል ይታወቃሉ፡፡

ደረቅ ቆሻሻ የሚለው ቃል ጠጣርና ከፊል ጠጣር የሆኑ ከምግብም ሆነ ከሌሎች የወዳደቁና ከአይነ ምድር ውጭ የሆኑትን የሚበሰብሱና የማይበሰብሱ ደረቅ ቆሻሻዎችን እንደ አመድ፣ የሞቱ እንስሳት፣ የተጣሉ የአትክልት የፍራፍሬ እና የመሳሰሉ ምግቦች ቅርፊቶችና የምግብ ትራፊዎች፣ ወዘተ… ያጠቃልላል፡፡ ደረቅ ቆሻሻ ከተለያዩ የመኖሪያና የስራ ቦታዎች፣ እንደ ፋብሪካዎች የንግድ ድርጅቶች፣ የገበያ ቦታዎች፣ ልዩ ልዩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ወዘተ.. ካሉ ቦታዎች ይፈጠራል፡፡ ቆሻሻ በተገቢው መንገድ ካልተሰበሰበ፣ ካልተከማቸ ካልተጓጓዘና ካልተወገደ የተለያየ ችግር ሊፈጠር ይችላል፡፡ ለዝንብ፣ ለአይጥ፣ ለትንኝና ልዩ ልዩ እንስሳት ምግብ፣ መራቢያና መጠለያ ከመሆኑም በላይ ለተላላፊ በሽታዎች መዛመት አመቺ ሁኔዎችን ይፈጥራል፡፡ መጥፎ ሽታ□ ከመፍጠርም ባሻገር የአካባቢውን ጥሩ ገጽታ ያበላሻል፡፡ ከጥንቃቄ ጉድለት የተነሣ ቆሻሻ ለማቃጠል የሚለኮሰው እሳት በንብረትና በሰው ሕይወት ላይ ጉዳት ያደርሳል፣ እንዲሁም ለውሃ ምግብና አየር መበከል አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

ፍሳሽ ቆሻሻ ከመፀዳጃ ቤት፣ ከምግብ ዝግጅት፣ ከገላና ልብስ እጣቢ፣ ከብት እርባታ□ አካባቢ፣ ከፋብሪካ፣ ለእርሻ አገልግሎት ከሚውል ማዳበሪያና የተባይ ማጥፊያ ኬሚካል እጣቢ ወዘተ ይፈጠራል፡፡ ፍሳሽ ቆሻሻ ባንድ ቦታ□ ሲከማች ወይም በተገቢው መንገድ ሳይያዝና ሳይወገድ ሲቀር ለዝንብና ትንኝ መራቢያ በመሆን ውሃን በመበከል እንደ ኮሌራና ታይፎይድ ለመሳሰሉት በሽታዎች መዛመቻ በመሆን ከፍተኛ የጤና ችግር ያስከትላል፡፡

በአጠቃላይ ደረቅም ሆነ ፍሳሽ ቆሻሻ እንደምንጩ ሁኔታ□ በማየትና የህብረተሰቡን ጤናና የመኖሪያ አካባቢን በማይጎዳና በማይበክል ሁኔታ□ መወገድ አለበት፡፡ ስለሆነም ይህን ችግር ለማቃለል ይህ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድና መጸዳጃ ቤት አዘገጃጀት ፓኬጅ ከጤና ኤክስቴንሽን ባለሞያዎች የሙያ ዝግጅቶችና ተልዕኮ ጋር ተጣጥሞ ተዘጋጅቷል፡፡

## 2. ዓላማ

### 2.1. አጠቃላይ ዓላማ

ተገቢ የሆነ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን ተግባራዊ በማድረግ አካባቢን ከብክለት በመከላከል ሊከሰቱ የሚችሉ በሽታዎችንና ሌሎች የጤና ጠንቆችን እንዲሁም ሞትን ለመቀነስ፣

### 2.2. ዝርዝር ዓላማ

- ዘላቂነት ያለው የተሻሻለ መፀዳጃ ቤት፣ የፈሳሽና ደረቅ ቆሻሻ አሰራር፣ አያያዝና አጠቃቀምን አስመልክቶ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ፣
- በእያንዳንዱ ቤተሰብ ነባራዊ ሁኔታን ያገናዘበና በአካባቢው በሚገኙ ቁሳቁሶች የተሻሻለ መፀዳጃ ቤት፣ የፈሳሽና ደረቅ ቆሻሻ ሰርቶ በንጽህና እንዲይዝና እንዲጠቀም ማድረግና፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀምን ማረጋገጥ፣

- እያንዳንዱ ቤተሰብ፣ ተቋምና ህብረተሰብ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻን በተገቢው መንገድ የማስወገድ ልምድ እንዲያዳብር ለማድረግ፣
- መኖሪያና መሥሪያ አካባቢዎች ለዝንቦች፣ ለትንኞች፣ ለአይጦችና ለልዩ ልዩ ጎጂ ነፍሳት ምግብ፣ መጠለያና መራቢያ እንዳይሆኑ ለማድረግ፡፡
- ደረጃዉን የጠበቀ ተስማሚ የሆኑ የሳኒቴሽን ቴክኖለጂዎች (አማራጮች) ለማስተዋወቅ

## 3. ቁልፍ መልዕክቶች

**ደረቅ ቆሻሻን ማከማቸት**

ከመኖሪያ ቤት ከተቋማት የሚወጡ ደረቅ ቆሻሻዎች እስኪወገዱ ድረስ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጁ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ እቃዎች እንዲቀመጡ ማድረግ፣

**የደረቅ ቆሻሻ ማከማቻ ዕቃዎች**

- በመኖሪያ ቤት እና ተቋማት ደረጃ ሊያገለግል የሚችል የቆሻሻ ማጠራቀሚያ እንደ ደረቅ ቆሻሻው ዓይነትና ይዘት ከማይሰነጠቅ ወይም ከማይሰበር ቁሳቁስ እንደ ቆርቆሮ፣ ፕላስቲክና ከመሳሰሉት በቀላሉ በአንድ ሰው ሊነሳ በሚችል አኳኋን ከተሰራ ማጠራቀሚያ መከማቸት፣
- እርጥበት የሌላቸው ሽታ የማያስከትሉ የደረቅ ቆሻሻ ዓይነቶች እንደ ወረቀትና የመሳሰሉትን ከቀርከሃ ከተሰራ ባለ ክዳን ሳጠራ ማጠራቀም
- ለድብልቅ ደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ የምንጠቀምባቸው መገልገያዎች በጥንቃቄ የተዘጋጁ ሆነው ማለትም ውሀ የማያፈሱ፣ የማይዝጉና ክዳን ያላቸው እንዲሆኑ ማድረግ ፣
- የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃዎች ሽታ እንዳያስከትሉ አንደአስፈላጊነቱ እንዲታጠቡ ማደረግ፣
- የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃ እርጥበታማ ባልሆነና ሌላ የጤና ችግር በማያስከትል ደረቅና ሊጨቀይ በማይችል ቦታ ላይ እንዲቀመጥ ማድረግ፡፡
- የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ሲመረጥ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡

**ደረቅ ቆሻሻን በቤተሰብ ደረጃ ማስወገድ ዘዴ**

- ከመኖሪያ ቤቱ በስተጀርባ ቢያንስ 10 ሜትር /20 ክንድ/ ርቀት እንዲኖረው ማድረግ፣
- የደረቅ ቆሻሻ መጣያ ቦታ ሲመረጥ የመሬት ተዳፋትነቱና የንፋስ አቅጣጫን /ንፋስ ከማስወገጃ ቦታው ወደ ቤት አቅጣጫ በማይነፍስበት/ ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡
- ከውሃ ጉድጓድ /መገኛ ቦታ/ በስተግርጌ በኩል በ30 ሜትር /60 ክንድ/ ርቀት እንዲኖረው ማድረግ፡፡

**የፌስታል አወጋገድ**

ፌስታል በአሠራሩ  የማይበሰብስ በመሆኑ ሳይቃጠል መሬት ላይ በሚጣልበት ጊዜ የአፈርን ለምነት በመቀነስ፣ ውሃ በመቋጠር፣ ለወባ ትንኝ መራቢያ አመች በመሆን፣ መጥፎ እይታን በመፍጠርና ከብቶች በሚውጡበት ጊዜ ሆዳቸውን በማሳበጥ ለሞት ስለሚዳርጋቸው በአወጋገዱ ላይ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት አስገዳጅ እየሆነ መጥቷል፡፡  ስለዚህ የሚከተሉትን እረምጃዎች መውሰድ ያስፈልጋል፡፡

- ❖ ፌስታልን እንዳለ ወደ ሜዳ ከመጣል ይልቅ ከሌሎች  ለማዳበሪያነት ከሚያገለግሉ ቆሻሻዎች ለይቶ መቅበር፣ ፌስታልና ሌሎች ላስቲኮችን እንስሳት ከበሉ እንደሚታመሙና ሊሞቱ እንደሚችሉ ማስረዳት፡፡
- ❖ ሁልጊዜ አዲስ ፌስታል ከመግዛት ይልቅ ቀደም ብለው የተጠቀምንበትን ፌስታል ምግብ ነክ ከሆኑ ሸቀጦች ውጭ ለሌላ  ዕቃዎች መያዣነት ማዋል፣
- ❖ ህብረተሰቡ ከፌስታል ይልቅ ሌሎች እንደ ወረቀት፣ የጨርቅ ከረጢት፣ ዘንቢል፣ ቅርጫት ወዘተ. የመሣሠሉትን ለዕቃ መያዣነት እንዲጠቀም ትምህርት መስጠት፡፡

**ፈሳሽ ቆሻሻ (Liquid Waste)**

በመኖሪያ ቤት የሚወጡ የፈሳሽ ቆሻሻ ዓይነምድርና ሽንት እንዲሁም ልዩ ልዩ እጣቢዎችና ፍሳሾች ናቸው፡፡

**ፈሳሽ ቆሻሻ የሚያስከትለው የጤና ችግር**

- ❖ መጥፎ ሽታ በመፍጠር ለተለያዩ መተንፈሻ አካላት(ለምሳሌ፡ አስም) በሽታዎች ያጋልጣል፣
- ❖ የመኖሪያ አካባቢ ውበትን ይቀንሳል፣
- ❖ ለትንኞችና ዝንቦች መራቢያ በመሆን የመኖሪያ አካባቢ ምቾትን ይቀንሣል በተጨማሪም ለተላላፊ በሽታ ሥርጭት አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል፣
- ❖ ፍሣሹ በጎርፍ አማካኝነት የአካባቢውን የውሀ መገኛ በመበከል የውሃውን ጥራት ይቀንሳል፣

**የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎች**

ምንም እንኳን ከተለያዩ ምንጮች የሚወጡ ፈሳሽ ቆሻሻዎች የተለያየ የማስወገጃ ዘዴ ቢኖራቸውም ፓኬጁ ሥራ ላይ ሊውል ከሚችልባቸው ቦታዎች አንጻርና አላማ በገጠር ያለውን የፈሳሽ ቆሻሻ በሚከተሉት ዘዴዎች ማስወገድ ይቻላል፡፡

**የአካባቢ ግብዓት በመጠቀም የተለምዶ መፀዳጃ ቤት መሥራት**

በሀገራችን በከተማም ሆነ በገጠር አካባቢዎች ጉድጓድ ቆፍረው ርብራብ አድርገውና ከለላ አበጅተው የሚጠቀሙበት አይነት መፀዳጃ ቤት የተለምዶ መጸዳጃ ቤት ይባላል፡፡

በተጨማሪም ህብረተሰቡ ተቀባይነት ያለው፣ አቅምን ያገናዘበ፣ ዘለቄታ ያለውና አቅመ ደካሞች፣ ህጻናት፣የአካል ጉዳተኞች ያማከለ መፀዳጃ ቤት መገንባት መቻል ያስፈልጋል፡፡

**የተሻሻለ መፀዳጃ ቤት ከተለምዶ የሚለይበት፡**

- የመፀዳጃ ቀዳደው ግጣም ያለው፤
- ወለሉ ለአደጋ የማያጋልጥና ከመፀዳጃ ቀዳዳው ዉጭ ሌላ ቀዳዳ የሌለው ፤
- ወለሉ የሚታጠብ/ሊጸዳ የሚችል፤
- በቂ ከለላ ያለውና ገመናን የሚሸፍን ፤
- ጣራ ያለው ፤
- የእጅ መታጠቢያ በአቅራቢያው ያለው፤
- የሰውን አማካይ ቁመት ግምት ውስጥ ያስገባ

**የመፀዳጃ ቤት የቦታ አመራረጥ**

- ለመጠጥና ለምግብ አገልግሎት ከሚውል ከማንኛውም አይነት የውሃ መገኛ ቢያንስ 30 ሜትር /30 እርምጃ/ ርቀት ኖሮት ከውሀ መገኛ አካሉ በስተግርጌ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፣
- በጤንነት ላይ ችግር እንዳይፈጥርና ምቾትን እንዳይቀንስ የንፋስ አቅጣጫውን በማጥናት ከመኖሪያ ቤት ቢያንስ 6 ሜትር /6እርምጃ/ ርቀት ላይ መሥራት፣
- ጥልቀቱ የከርሰ ምድር ውሀን እንዳይበክል ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፣
- መፀዳጃ ቤቱ ነፋስ እንደ ልብ ሊዘዋወር በሚችልበት አካባቢ መሠራት አለበት፣
- ማስመጠጥ የማይቻልበት አካባቢ ከሆነ መፀዳጃ ቤት ሲሞላ ሌላ መሥራት እንዲቻል ቦታ ማዘጋጀት፣
- ለህዝብና ለተቋሞች አገልግሎት የሚውል መፀዳጃ ቤትን ተጠቃሚው በቀላሉ ማየት በሚችልበት አመቺ ቦታ መሥራት ያስፈልጋል፣
- መፀዳጃ ቤቱ ሲሞላ ለማስመጠጥ አመቺ መንገድ መኖሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፣
- መፀዳጃ ቤት የሚገነባበት ቦታ ውሀ የማይቋጥርና ጎርፍ የማይገባበት መሆን አለበት፣

ሽታ አልባ መፀዳጃ ቤት ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን መመሪያዎች ተከትሎ ከተዘጋጀ ቀደም ብሎ ከተጠቀሰው የመፀዳጃ ቤት ዓይነት ጥቅም በተጨማሪ የሚከተሉት ጥቅሞች ይኖሩታል፡-

- መጥፎ ሽታ አይኖረውም፣
- ዝንቦች አይራቡበትም፣ ጉድጓዱ ውስጥ የሚገቡትን እንዳይወጡ ስለሚያደርግ እዚያው ይሞታሉ፣
- የመቀመጫ ቀዳዳው የተመጠነ ሆኖ ስለሚዘጋጅ በልጆችም ሆነ በአዋቂዎች እንዲሁም በቤት እንስሳት ላይ አደጋ አያስከትልም፣
- በውኃ ከሚሰራ መፀዳጃ ቤት ጋር ሲነፃፀር ወጪውም ሆነ አሰራሩ በጣም ቀላል ነው፣ ለንጽህና አጠባበቅም አመቺ ነው፡፡

**ጊዜያዊ መፀዳጃ ቤት**

ጊዜያዊ መፀዳጃ ቤት ሰዎች በሰፈራ ምክንያት፣ በጦርነት፣ በወረርሽኝ፣ በጤና መታወክ ጊዜ እንዲሁም በአንዳንድ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ችግሮች ምክንያት መኖሪያ ቀያቸውን ለቀው በአንድ አካባቢ በሚሰባሰቡበት ጊዜ ለጥቂት ቀናት ብቻ ሊያገለግል የሚችል ነው፡፡

**አሠራሩ**

- ስፋቱ አንድ ክንድ /ግማሽ ሜትር/ ጥልቀቱ ሁለት ክንድ /አንድ ሜትር/ ርዝመቱ እንደተጠቃሚው ብዛት የሚሆን ጉድጓድ መቆፈር፣
- ጉድጓዱ በሚቆፈርበት ጊዜ ስፋቱና ጥልቀቱ ከላይ የተገለጸው ሆኖ ርዝመቱ ለ500 ተጠቃሚዎች፣ በ10 ሜትር ስሌት መሠራት አለበት፣
- ከጉድጓዱ የሚወጣውን አፈር በአንዱ አቅጣጫ ከጉድጓዱ አጠገብ መቆለል፣
- አካፋ፣ ወይም ጠፍጣፋ ድንጋይ፣ እእንጨት ወይም የእንጨት ቅርፊት አፈሩን ለመመለሻነት ማዘጋጀት፣
- ከተጠቀሙ በኂላ ከበስተኂላ የተቆለለውን አፈር በመመለስ ዓይነ ምድሩን ማዳፈን፣
- ዓይነምድሩ ሙሉ በሙሉ በአፈር ለመከደኑ ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡  ይህም ዝንቦች በዓይነምድሩ ላይ ለማረፍ ዕድል እንዳያገኙ ለማድረግ ይረዳል፣
- ጉድጓዱ ሲሞላ አንድ ስንዝር /20 ሣንቲ ሜትር/ ያህል ሲቀረው ሙሉ በሙሉ ተደፍኖ ሌላ ተመሳሳይ ጉድጓድ መቆፈር አለበት፡፡
- የጉድጓዱ ዙሪያ ሕጻናትና እንስሳት እንዳይገቡበት በአካባቢው በሚገኝ ቁሳቁስ መታጠር አለበት፡ ፡
- ከውሃ መገኛ ቦታዎች ቢያንስ 30 ሜትር ያህል መራቅ ይኖርበታል፡፡

**የማስረገያ ጉድጓድ**

ከገላ፣ ከእጅ፣ ከልብስና ከእጅ እጣቢ የወጣውን ፈሳሽ ቆሻሻ አካባቢን በማይበክል ሁኔታ ለማስወገድ የምንጠቀምበት ዘዴ ነው፡፡

**ከመኖሪያ ቤት ውስጥ የሚወጣ የፍሳሽ ማስረጊያ አሠራር**

- የፍሳሽ ማስረጊያ ቦታ ከመኖሪያ ቤት ቢያንስ 10 ሜትር /20 ክንድና/ ከውሃ መገኛ 30 ሜትር መራር ይኖርበታል
- 1 ሜትር /2 ክንድ/ ስፋት፣ 1 ሜትር /2 ክንድ/ ቁመት 1 ሜትር /2 ክንድ/ ጥልቀት ያለው ጉድጓዳ መቆፈር፣
- እስከ 40 ሳ.ሜ ያለውን ገደል ከታች ወደላይ በኮረት /ስብርባሪ ድንጋይ/ መሙላት
- ከኮረቱ ቀጥሎ 30 ሳ.ሜ /አንድ ስንዝር ተኩል/ ወደ ላይ የሚሆነውን ቦታ በትናንሽ ጠጠሮችና በአሸዋ መሙላት
- ቀሪው 30 ሳ.ሜ. /አንድ ስንዝር ተኩል/ ላይ ከስር የተበሳ እንስራ ከጉድጓዱ መካከል ላይ በማስቀመጥ ቀሪውን የጉድጋድ አካል በአሸዋና በጠጠር መሙላት፡፡ ቅባትና ጠጣር የሆኑ ነገሮችን ለማስቀረት የእንስራው የውስጥ አካል በሣር ቢሞላ ጥሩ ነው
- የእንስራውን አፍ በተበሳሳ ቆርቆሮ መግጠም፣

**መፀዳጃ ቤት ሠርቶ በመጠቀም**

የሰው ዓይነ ምድርና ሽንትን በመፀዳጃ ቤት አያያዝና አጠቃቀም ፓኬጅ በተገለፀው መሠረት መፀዳጃ ቤት ሰርቶ በአግባቡ በመጠቀም ዓይነምድር ወለድ በሽታዎችንና ብክለትን መከላከል ይቻላል፡፡

**የመፀዳጃ ቤት ጠቀሜታ**

በአግባቡ በተደራጀ መፀዳጃ ቤት መጠቀምና ዐይነ ምድርን በጉድጓድ ወስጥ እንዲቀበር ማድረግ የሚከተሉት ጥቅሞች አሉት፡፡

# 4. የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድና መጸዳጃ ቤት አዘገጃጀት አያያዝና አወጋገድ ፖኬጅ በሚመለከት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

## 4.1. የቀበሌውን መረጃ መሰብሰብ

- በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ መረጃዎችን ማሰባሰብ ፣መተንተንና ማጠናቀር
  - የተሻሻለና ያልተሻሻለ መፀዳጃ ቤት ያላቸው ቤተሰቦች ብዛት
  - መፀዳጃ ቤት በአግባቡ የሚጠቀሙና የማይጠቀሙ ቤተሰብ ብዛት
  - ከሜዳ ላይ መፀዳዳት ነጻ የሆኑ ጎጦች/መንደሮች ብዛት
  - መፀዳጃ ቤት ለመሥራት ያልቻሉበትን ምክንያት ለይቶ ማወቅ
  - የደረቅና ፍሳሽ ማስወገጃ ያለቸውና የሌላቸው ቤተሰቦች ብዛት
- በተጠናቀረው መረጃ መሰረት ችግሮችንና ቅድሚያ የሚሠጣቸውን ተግባራት መለየት

## 4.2. በመረጃው የተሰበሰበውን ውጤት ለህብረተሰቡ መግለጥና በጋራ የሥራ እቅድ ማውጣት

- በመረጃው የተገኘውን ውጤቱን ለህብረተሰቡ መግለጥና በውጤቱ ዙሪያ ከህብረተሰቡ ጋር መወያየት
- ቅድመ ጥናቱን መሠረት ያደረገና ህብረተሰቡን ያሳተፈ የሥራ እቅድ ማውጣት
- እንደ አስፈላጊነቱ የሳምንት፣ የወር፣ የሩብ ዓመት፣ የግማሽ ዓመትና የዓመት የሥራ እቅድ ማውጣት፣

## 4.3. በተሻሻለ መፀዳጃ ቤት፣ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ላይ ስለጠና መስጠት

- በዚህ ስልጠና የሚሳተፉ የልማት ቡድን መሪ፣ የ1ለ5 መሪዎች፣የወንዶች የ1ለ5 መሪዎች፣ስትሪንግ ኮሚቴ/ኮማንድ ፖስት፣የሃይማኖት መሪዎች ይሆናሉ ።

## 4.4. ለፓኬጁ ስራ ደጋፊ ሊሆኑ ከሚችሉ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ ተቋማት፣ ማኅበራዊ ተቋማት፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ቅንጅት በመፍጠር፣

- በቀበሌው የሚገኙትን ባለድርሻ አካላትን መለየት
  - መስተዳድር - አስተዳደራዊ ድጋፍ እንዲሰጥ፣
  - ግብርና - የልማት ሰራተኞች ትምህርትና ድጋፍ እንዲሰጡ
  - ትምህርት - ለመምህራንና ተማሪዎች ትምህርት በመስጠት የአካባቢውን ህብረተሰብ እንዲያስተምሩ፣ ሞዴል በመሆን ወዘተ..፣

- ማህበራት (የሴቶች፣ የወጣቶች ወዘተ)- በማመቻቸት፣ አባላቶቻቸውን በማንቀሳቀስና በማሳተፍ …፣
- የሀይማኖት ተቀማትና የጎሳ መሪዎች - በማመቻቸት፣ አማኞቻቸውን በማንቀሳቀስና በማሳተፍ …፣

❖ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች - በቴክኒክና በቁሳቁስ ወዘተ. በመደገፍ

❖ የተሰበሰበውን መረጃ መሰረት በማድረግ ቀበሌው ያለበትን ሁኔታ መተንተንና ከላይ ለተዘረዘሩት ድጋፍ ሰጭ አካላት ማቅረብ

❖ በቀረበው መረጃ መሰረት በማድረግ ውይይት ማካሄድ፣ የጋራ ስምምነት ላይ መድረስና በትብብር ሊሰሩ የሚችሉ ስራዎችን በመለየት አብሮ ለመስራት ማቀድ፡፡

## 4.5. ህብረተሰቡን በማስተማር፣ በማስተባበር፣ በመቀስቀስ ተሳትፎውን በማሳደግ የባህሪ ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ፤

❖ በቤተሰብ ደረጃ ስለ ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሰፊና ቀጣይነት ያለው ትምህርት መስጠት፡፡

❖ በስብሰባ፣በ1ለ5 እና ልማት ቡድን ውይይት፣ በዕድር በሐይማኖት ቦታዎች፣ በህዝባዊ በዓላት በትምህርት ቤቶች ወዘተ ስለ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ትምህርት መስጠት፣

**ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻን በአግባቡ ባለማስወገድና መጸዳጃ ቤት ባለመጠቀም የሚፈጠሩ የጤና ችግሮችና የመከላከያ ዘዴዎች**

<table>
<tr><th>ተራ ቁጥር</th><th>የሚከተሉ ችግሮች</th><th>ሊከሰቱ የሚችሉ በሽታዎች</th><th>መከላከያ</th></tr>
<tr><td>1</td><td>የአካባቢ መበከል አፈር፣ውሃ፣ከባቢ አየር፣ምግብ</td><td>ቢጫወባ፣ኮሌራ፣ ቢልሀርዚያሲስ፣ የአንጀት ተስቦ፣ የመተንፈሻ አካል በሽታዎች</td><td rowspan="4">❖ ደረቅ ቆሻሻን በአግባቡ ማስወገድ አበስብሶ ለማዳባሪያነት እንዲሁም ለባዮጋዝ መጠቀም<br>❖ ጉድጓድ ውስጥ በመቅበር በተመረጡ ቦታዎች አከማችቶ በማቃጠል በግቢ አካባቢ በጥንቃቄ በማቃጠል<br>❖ ኢንሲነሬተር በመጠቀም በቆሻሻ ክምችት ምክንያት የእሳት አደጋ እንዳይከሰት ጥንቃቄ ማድረግ<br>❖ በተመረጡ ቦታዎች አከማችቶ በአግባቡ ማዳፈን ወይም ማቃጠል<br>❖ ፍሳሽ ቆሻሻን በአግባቡ ማስወገድ መሬት ውስጥ በማስረግ ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ሲስፑል በመጠቀም</td></tr>
<tr><td>2</td><td>ልዩ ልዩ ዝንቦች፣ ትንኞችና፣ አይጦች መራባት</td><td>ተቅማጥ፣ ተስቦ፣ ትራኮማ ወዘተ</td></tr>
<tr><td>3</td><td>መጥፎ ሽታ መፍጠርና አካባቢ ለእይታ ጥሩ አለመሆን</td><td>የመተንፈሻ አካል፡ አስም በሽታዎች ያባብሳል ጭንቀትን ይፈጥራል</td></tr>
<tr><td>4</td><td>የቃጠሎ አደጋ ማድረስ</td><td>የንብረት መጥፋት በሰውነትና በሕይወት ላይ አደጋ ማድረስ</td></tr>
</table>

## 4.6. ከአይነምድር ነፃ የሆነ ቀበሌ/መንደር/ጎጥ መፍጠር

- ❖ በቀበሌው ውስጥ በየሜዳው መጸዳዳት የሚበዛባቸውን መንደሮች መለየት
- ❖ ከጤና ጣቢያው ባለሙያዎች ጋር በመሆን የማቀጣጠል ስራ ለመስራት ማቀድ
- ❖ የማቀጣጠል ስራዎች ለማከናወን የስበሰባ ጊዜ በመወሰን ህብረተሰቡ ለስብሰባ እንዲመጣ መቅጠር ፡፡
- ❖ ከማቀጣጠል በኋላ የተግበራ ክትትል ከልማት ቡድን መሪዎችና ከኮማንድ ፖስት ጋር በመሆን ክትትል ማድረግ፡፡
- ❖ ሁሉም ቤተሰብ መጸዳጃ ቤት ሰርቶ መጠቀም ሲጀምርና መንደሩ ከአይነምድር ነፃ መሆኑ ሲረጋገጥ ያሳውጃሉ፡፡

- መንደሩ/ጎጡ ወደ ሃላ እንዳይመለስ ጥብቅ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፡፡

## 4.7. የተሻሻለ መጸዳጃ ቤትን ኅብረተሰቡ እንዲሠራ ለማድረግ አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን ማስተዋወቅ

- በሳኒቴሽን ቴክኖሎጂ ግብዓቶች ላይ የትምህርትና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን መሥራት
- ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በመተባበር ከሳኒቴሽን ቴክኖሎጂ አምራቾች ጋር ህብረተሰቡን ታገናኛለች
- የሳኒቴሽን ግብዓቶች በሌሉባቸው አካባቢዎች በአካባቢው በሚገኝ ቁሳቁስ እንዲሠሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን መሥራት
- ከጥቃቅንና አነስተኛ እንዲሁም ከሌሎች ሴክተር ጽ/ቤቶች ጋር በመተባበር ጉዳዩ ለሚመለከታቸው በሳኒቴሽን ቴክኖሎጂ አማራጮች ላይ ስልጠና እንዲያገኙ ማስተባበር

## 4.8. ሰርቶ ማሳያ ዘዴ በመጠቀም ዘላቂነት ያለው የተሻሻለ መፀዳጃ ቤት አሰራርና የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ክህሎትን ማስጨበጥ

- የጤና ኤክስቴንሽን ባለሞያ በማሰልጠኛ ተቋማት ውስጥ ተሰርተው የሚገኙትን የሠርቶ ማሳያ ሞዴሎች በአርሶአደር ማሰልጠኛ በመሥራትና ያንኑ በቀበሌው ከሚገኙ ትምህርት ቤቶችና ሊረዷት ከሚችሉ ተቋማት ጋር በመተባበር ኅብረተሰቡ እንዲተገብር ማስተማርና ማመቻቸት ይኖርባቸዋል፡፡
- ህብረተሰቡ በቀላሉ አይቶ ስለ ደረቅና ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አሠራር እንዲረዳ ሰርቶ ማሳያ በመሥራት ቤተሰቦች በራሳቸው እንዲሠሩ ማስቻል፣

## 4.9. መልካም ተሞክሮን ማስፋፋት

- የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ ጥሩ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ቤተሰቦችን በመለየት መቀመር
- የ1ለ5 መሪዎች በጎረቤቶች መካከል የልምድ ልውውጥ እንዲካሄድ ያደርጋሉ፡፡
- በተጨማሪም አመርቂ ውጤት ላመጡ ልማት ቡድን በመምረጥ ሌሎች የልማት ቡድኖች እንዲጎበኙ በማድረግ ተሞከሮውን እንዲያሰፉ ማስቻል፡፡
- በቀበሌ ደረጃ ተቀባይነትና ተሰሚነት ያላቸውን ግለሰቦች እና የልማት ቡድን መሪዎች ጥሩ ሥራ ወደተሰራበት ቀበሌ በመውሰድ ማሳየት
- ተሞክሮ ልውውጡን መሰረት በማድረግ በእያንዳንዱ ልማት ቡድን የሚሰሩ ስራዎችን መለየትን ማቀድ እንዲሁም ትግበራዉን መከተተል፡፡

## 4.10. የማነቃቂያ ዘዴዎች በመጠቀም አመርቂ ውጤት ላመጡ አባዎራዎችና ልማት ቡድኖች ማበረታታቻ መስጠት

- በፖኬጁ ጥሩ ተሳትፎና እንቅስቃሴ ላደረጉ ቤተሰቦች ከልማት ቡድን መሪዎችና ከኮማነድ ፖስት ጋር በመሆን የመምረጫ መስፈርት በመጠቀም ለሽልማት የሚበቁትን መለየት
- የማነቃቂያ ስጦታዎች መሸለም፣
  - የምስክር ወረቀት
  - ቀለል ያሉና አሳቂ እንደ ሳሙና ያሉ በአካባቢው በቀላሉ የሚገኝ ቁሳቁስ
  - በስብሰባ ላይ እንደ ምሳሌ መጥቀስ ወዘተ

## 4.11. አካባቢያዊና ሕጋዊ ደንቦችን በመጠቀም፣

- አዳዲስ ቤት የሚሰሩና ቤታቸዉ በአዲስ የሚቀይሩ ቤተሰቦች በሚኖሩበት ጊዜ መፀዳጃ ቤት መገንባት እንደአንድ መስፈርት እንዲታሰብ ከቀበሌ አመራር ጋር በመሆን የአከባቢ ህግ/ደንብ ማዉጣት
- የአካባቢያዊ ሕጐችን- ከመንግሥት ሕግና ደንቦች ጋር አጣጥሞ መሥራት፣
- የአካባቢው ነዋሪ በጋራ በሚወሰነው መተዳደሪያ ደንብ እንዲያውቅ ማድረግ
- በመንግሥት የሚወጡ ህጐችን ተግባራዊ ማድረግ፣

# 5. አገልግሎቱ ለመሰጠት የሚያስፈልጉ ግብአቶት

## 5.1. ማጣቀሻዎች

- በትምህርት ቤት የደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ ማጣቀሻ መፅሀፍ
- የጤና ልማት ሰራዊት ማሰልጠኛ ማንዋል
- ፖስተር
- በራሪ ወረቀቶች
- የተዘጋጀ ቼክሊስት/መጠየቅ

## 5.2. ቁሳቁሶች

- የተለያየ ቀለም ያላቸው የጤና ኬላ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ባልዲዎች
- ሜትር
- ሎግ ቦክ (መከታተያ ቅጽ)

## 1. ከጤና ጣቢያ ጋር አብሮ መስራት

የጤና ጣቢያ ባለሞያዎች በተለይም የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ባለሙያ መረጃ አሰባሰብ፣ በቀበሌ ደረጃ ሊወጡ የሚገቡ ህጎችን በማርቀቅና ተሞክሮዎችን በመለየት በመቀመርና በማስፋት አብረው ያቅዳሉ ይሰራሉ፡፡ የልማት ቡድን አመራር ስልጠና ጊዜ ሙያዊ እገዛ ያደርጋሉ፡፡ ለዚህም፡

- ❖ እገዛ የሚያስፈልገውን ክፍተት መለየት
- ❖ የጤና ባለሙያዎችን ቴክኒካዊ እገዛ መጠየቅ ለምሳሌ ከአይነ ምድር ነፃ ሆነ ቀበሌ ለመፍጠር የማቀጣጠያ ዉይይት መምራት
- ❖ በጋራ ተባብሮ መሥራት ማለትም ቀበሌ በመከፋፈል ቀጥተኛ የሆነ ቴክኒካዊ ድጋፍ እንዲሰጡ ማድረግ፣

## 6. ክትትልና ግምገማ

- ❖ ፓኬጁ በአግባቡ መተግበሩን በሥፍራው በመገኘት ክትትል ማድረግና ሙያዊ ድጋፍ መሥጠት ይጠበቅባታል፡፡
  - ○ ይህም ማለት መጸዳጃ ቤት እና እጅ መታጠቢያ መሥራታቸውን፣ በአግባቡ መያዛቸውንና መጠቀማቸውን እንዲሁም ማሻሻላቸውን መከታተል፡፡
  - ○ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ማዘጋጀታቸውን መከታተል ያስፈልጋል፡፡
  - ○ ወርሀዊ የልማት ቡድን ዉይይት ላይ አዲስ የተሰሩ ፣ መሻሻል የተደረገባቸዉ መፀዳጃ ቤቶችና ደረቅ ቆሻሻ ማሰወገጃዎች መረጃ መሰብሰብ
- ❖ የኘሮግራሙ አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎች መሳካታቸውን ማረጋገጥ
- ❖ ዓላማዎቹን ለማሣካት የተዘጋጀ ዝርዝር ዕቅዶች መፈጸማቸውን መመልከት

## 7. የሚጠበቁ ውጤቶች

- ❖ የመጸዳጃ ቤት አዘገጃጀትና የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ላይ የህብረተሰቡ እወቀትና ክህሎት ይዳብራል፣
- ❖ ህብረተሰቡ በግልና በጋራ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃና መጸዳጃ ቤት በማዘጋጀት የመጠቀም ልምድ ይዳብራል፣
- ❖ ስልጠና በመስጠት ለፓኬጅ ሠራተኛዋ ድጋፍ የሚሰጡ ተጨማሪ የህብረተሰብ ክፍሎች ይፈጠራሉ፣
- ❖ የቅንጅታዊ አሠራር ባህል ይዳብራል፣
- ❖ በደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻና መጸዳጃ ቤት አዘገጃጀትና አያያዝና ላይ ከእቅድ ማውጣት እስከ ማስፈፀም ድረስ የህብረተሰቡ ተሳትፎና ልምድ ይዳብራል፣

- ቀበሌዉ የደረቅ እና ፈሳሽ ቆሻሻና መጸዳጃ ቤት አዘገጃጀት ተስማሚ የሆኑ ቴክኖለጂዎች ይኖሩታል
- ከአይነምድር ነፃ  የሆኑ ጎጦች ይፈጠራሉ ፡፡

## 8. ድጋፋዊ ክትትልና ግምገማ መለኪያዎች

- ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻና መጸዳጃ ቤት አዘገጃጀትና አያያዝ አስመልክቶ ትምህርት የተሰጣቸው ሰዎች ብዛት ሴት፣ ወንድ፣
- ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻና መጸዳጃ ቤት አዘገጃጀትና አያያዝ አስመልክቶ የተደረጉ ስብሰባዎች ብዛት፣
- ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻና መጸዳጃ ቤት አዘገጃጀትና አያያዝ አስመልክቶ ሥራ ላይ የዋሉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዓይነት ብዛት፣
- የተሻሻለ የግልና የጋራ መጸዳጃ ቤት ያላቸው ቤተሰቦች ብዛት
- ባዮጋዝ ያዘጋጁ ቤተሰቦች
- በመፀዳጃ ቤቱ አጠገብ የእጅ መታጠቢያ ውሃና ሳሙና ያላቸዉ ፣
- ከኣይነምድር ነፃ የሆኑ ጎጦች ብዛት
- መፀዳጃ ቤቱ ከማዕድ ቤትና ከውሃ መገኛዎች በተገቢው ርቀት ላይ መሆኑን